# የአንዳርጋቸው ጉዳይ

ግርማ ካሳ

May 12, 2018

አንዳርጋቸው በአገዛዙ ላይ የትጥቅ ትግል አውጃለሁ ያለውና ከሻእቢያ ጋር የሚሰራው ግንቦት ሰባት የተባለው ድርጅት ዋና ጸሃፊ ነበር። ወደ አስመራ ሲሄድም ነበር የመን ላይ የወያኔ ደህንነቶች ከየመኖች ጋር በመተባበር አፍነው የወሰዱት።

አንዳርጋቸው ጽጌ የእንግሊዝ ዜግነት ያለው ሲሆን የእንግሊዝ ኤምባሲም የርሱን ጉዳይ፣ ደህንነቱን በተመለከተ፣ በቅርበት እየተከታተለ እንደሆነ ይገልጻል። ሆኖም የእንግሊዝ መንግስት ለአመታት ወያኔን ሲደገፍ የነበረ መንግስት እንደመሆኑ ፣ ሌሎች የሕሊና እስረኞች ሲፈቱ አንዳርጋቸውን አለማስፈታቱ ለብዙዎች ጥያቄ እየሆነ ነው።

የአንዳርጋቸው ጽጌ ድርጅት ግንቦት ሰባት የተንኮታኮተ ድርጅት ነው። የዉሸት ድርጅት እንደሆነ አገር ሁሉ ያወቀው ጉዳይ ነው። አንዳርጋቸው ጽጌ ቢፈታ አንደኛ ተመልሶ ግንቦት ሰባትን አይቀላቀልም። ይሄንንም የምልበት ምክንያቶች አሉኝ። ካስፈለገም ምክንያቶች መዘርዘር እችላለሁ። ቢቀላቀልም ደግሞ የሚያመጣው ምንም ፋይዳ አይኖርም። ያንንም ወያኔዎች በሚገባ ያውቁታል። አምስት ሳንቲም ግንቦት ሰባትን አይፈሩም። ታዲያ ለምንድን ነው አንዳርጋቸው ጽጌን የማይፈቱት ?

አንደኛ – ወያኔዎች በባህሪያቸው በጣም ቂመኛ ናቸው። አንዳርጋቸው ጽጌ ከነርሱ ጋር ይሰራ ፣ የኢሕአዴግ ከፍተኛ አመራር የነበረ ነው። ከነርሱ ጋር የነበረ ሰው እነርሱን መቃወም ሲጀምር ሰዎቹ አለመደሰት ብቻ ሳይሆን ያበሳጫቸዋል። በመሆኑም የአንዳርጋቸው መፈታት ጉዳት ባያመጣባቸው ከቂም የተነሳ የመፍታት ፍላጎት ላይኖራቸው ይችላል።

ሁለተኛ – ኮሎኔል ደመቀ ዘዉዱ፣ እነ ጀነራል አሳምነው ጽጌ ያሉትን ፈተው የለም ወይ ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። እነ ኰሎኔል ደመቀ እንዲፈቱ ብአዴን ትልቅ ጫና አድርጓል። ወያኔዎች ባይፈልጉም እነ ኮሎኔል ደመቀ እንዲፈቱ፣ እነ ገዱ አንዳርጋቸው ፣ ስላስገደዱ ነው የተፈቱት። አንዳርጋቸው ጽጌ በኢሕአዴግ ውስጥ የሚሟገትለት አካል የለዉም። ብአዴኖች በሕወሃቶች ግንቦት ሰባቶች ናችሁ ተብለው ስለሚከሰሱ፣ ያንን ክስ ለማጠናከር አንዳርጋቸው ይፈታ ብለው ለመከራከር ይከብዳቸዋል። ያ ብቻ አይደለም ብዙ የአማራ ክልል ተወላጆች ከግንቦት ሰባት ወጥተዋል። ግንቦት ሰባት በብአዴኖች ዘንድም ብቻ ሳይሆነ በክልሉ ባሉ ነዋሪዎች ዘንድ ተወዳጅ አይደለም።

ሶስተኛ – ይሄ በኔ እይታ ዋናውና ትልቁ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም ብዬ አስባለሁ። አንዳርጋቸው ጽጌ እንዴት እንደታሰረ ሁላችንም የምናውቀው ነው። አንዳርጋቸው ከመታሰሩ በፊት አንዳንድ መረጃዎች ነበሩኝ። አንዳርጋቸው በሻእቢያ ደስተኛ አልነበረም። ሻእቢያዎች በተቃዋሚዎች ስም ብዙ ገንዘብ እየሰበሰቡ ለተቃዋሚዎች የሚሰጡት ፍርፋሪ ነበር። በተቃዋሚዎች

ስም ቢዝነስ ይሰሩ ነበር። ብዙ አመት አስመራ ከተመላለሰና ከደከመ በኋላ አንዳርጋቸው ተስፋ ወደ መቁረጥ የደረሰበት ሁኔታ እንደነበረ ነው የሰማሁት።

ከአንዳርጋቸው ጋር በቅንጅት ድጋፍ ማህበራት ውስጥ ሰርቼ አውቃለሁ። በኋላ በወሰደው አቋም ባልስማም፣ ብቃወመውም፣ አንዳርጋቸው የስራ ሰው ነበር። ከተሳሳተ፣ እየሄደበት ያለው አካሄድ ትክክል ካልሆነ ለመታረም ፍቃደኛ የሆነ ሰው ነው። በተለይም ደግሞ አንድ የማደንቅለት ነገር አደርባይ አይደለም። አይዋሽም። አንድ ምሳሌ ላስታወሳችሁ። ግንቦት ሰባት በኤርትራ በኩል ትግል ለማድረግ ሲወስን ወደ ዚያ በመጀመሪያ የሄደው አንዳርጋቸው ነበር። ያኔ የኢትዮጵያ ሪቪው አንዳርጋቸው አስመራ እንደሆነ ዘገበ። የግንቦት ሰባት ሊቀመንበር ዶር ብርሃኑ ነጋ በአዲስ ድምጽ ራዲዮ ቀርበው ፣ በይፋ፣ በአደባባይ፣ ሽምጥጥ አድርገው ዋሹ። "አንዳርጋቸው ኤርትራ አይደለም" ብለው። ብዙም አልቆየም ቺካጎ ከተማ በተደረገ ስብሰባ አንዳርጋቸው ሲጠየቅ "አዎን አስመራ ነበርኩ " ብሎ እዉነቱን ለሕዝብ ተናገረ። እንደ ዶር ብርሃኑ ለማጭበርበር አልሞከረም። አንድ ነገር አውቃለሁ። አንዳርጋቸው ባሉት የፖለቲካ አቋሞች ላንስማማ እንችላለን፤ ግን ያመነበትን እዉነቱን ነው የሚነገረን። ኢንቴግሪቲ ያለው ሰው።

ሻእቢያን ባለው ነገር አንዳርጋቸው ደስተኛ እንዳልሆነ፣ ግንቦት ሰባትን ከሻእቢያ ጥገኝነት ለማውጣት እንደዳዳው ጠንቅቀው አውቀዉታል። ከለንደን ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ኤርትራ ሲመጣ የፍላይት ኢንፎርሜሽኑን የሚያወቁት እንግሊዞችና ሻእቢያዎች ብቻ ነበሩ። እንግሊዞች የራሳቸውን ዜጋ አሳልፈው ይሰጣሉ ማለት የማይታሰብ ነው። ያንንም የሚያደረጉበት ምንም ምክንያት የላቸውም። ስለዚህ አንዳርጋቸው በየመን በኩል አድርጎ እንደሚመጣ ለወያኔ አስቀድመው መረጃ የላኩት ሻእቢያዎች ናቸው። መረጃው ወያኔዎች እንደደረሳቸው፣ ከየመን መንግስት ጋር ተነጋግረው፣ እዚያ ነው ኤርፖርት ቁጭ ብለው ጠበቁት። በጥቂት ሰዓታት ውስጥ አንዳርጋቸውን አፍነው ወደ አዲስ አበባ ሄዱ።

አንዳርጋቸው ቢፈታ ይሄንን ሁሉ መናገሩ፣ ማጋለጡ የማይቀር ነው። ወያኔዎች ከሻኢቢያ ደህንነቶች ጋር ያላቸው ሚስጥራዊ ግንኙነት እንዲጋለጥባቸው አይፈለጉም። ለዚህ ነው አንዳርጋቸውን መፍታት የማይፈለጉት።

ሆኖም ግን የዶር አብይ አስተዳደር በደህንነት መስሪያ ቤት ውስጥ ያሉ ወያኔዎች አቅምና ሃይል ማዳከም ከቻለ ግን፣ ምን አልባት አንዳርጋቸውን የመፍታት እድሉ ከፍ ሊል ይችላል። ይሄም እንዲሆን እንዳርጋቸው ጽጌ ይፈታ ዘንድ ሁላችንም የድርሻችንን ማድረጉ አስፈላጊ ነው።

አንድ ነገር አንርሳ፣ አንዳርጋቸው ምንም እንኳን ወደ ትጥቅ ትግል መሂዱና ከሻእቢያ ጋር ለመስራት መሞከሩ ትክክል ባይሆንም፣ በወቅቱም ብንቃወመዉም፣ ያንን ያደረገው ለአገርና ለሕዝብ ብሎ ነው። በለንደን የተመቻቸ የተደላደለ ኑሮ የነበረው ሰው ነበር። ግን እኔ ቢደላኝም፣ በአገሬ ህዝብ አንገቱን ደፍቶ ሙብቱ ተረግጦ መኖር የለበትም በሚል ነው፣ የዜጎች ሕመም ሕመሙ ሆኖ ትግሉን የተቀላቀለው። እኔ በግሌ ከራሱ አልፎ ለሌላው የሚቆረቆር፣ ለሌላው መስዋትነት ለመክፍል ለተዘጋጀና በተግባር ላሳየ ሰው ትልቅ ክብር አለኝ።

ሌላው ግንቦት ሰባትን ከተቀላቀለ በኋላ ያለውን እንተዉወና፣ ግንቦት ሰባትን ሳይቀላቀል በፊት በቅንጅት ውስጥ እንዳርጋቸው ያደረጋቸው በርካታ ትላልቅ ቁም ነገሮችን መርሳትም የለብንም። መጽሃፍ ጽፎ፣ የሽያጩን ገቢ ለራሱ ከማድረግ ለትግሉ ያበረከተ ትልቅ ሰው ነው። ማን ነው እንደዚያ የሚያደረገው ? ሌላ የማወቀው ሰው አቶ ስዬ አብርሃን ነው፤ መጽሀፍ ጽፎ የመጽሃፉን ገቢ ለአንድነት ፓርቲ ያበረከተ።

የአንዳርጋቸው መፍታት አንደኛ ከሰብአዊነት አንጻር፣ ሁለተኛ ብሄራዊ መግባባትን ከማስፈን አንጻር አስፈላጊ ነውና፣ አንድርጋቸው ጽጌ ይፈታ ዘንድ ጥሪዬን አቅርባለሁ።

አንዳንድ ያልተረጋገጡ መረጃዎች አሉኝ። ዶር አብይና አቶ ደመቀ መኮንን የሕወሃት የደህንነት ሃላፊዎች ግትርነት በመቋቋም አንዳርጋቸውን ለመፍታት ፍላጎት እንዳለቸው ሰምቻለሁ። እዉነት ያድርገው ብዬ እዚህ ላይ አቆማለሁ።

(በነገራችን ላይ አገር ቤት ያሉ በሰላም የሚታገሉ ድርጅቶች፣ አንድራጋቸው በቅንጅት ጊዜ ያደረገውን አስተዋጾ ከግምት በማስገባትና ከሰብ አዊነት በመነሳት፣ ከአንዳርጋቸው የትግል ስትራተጂ ጋር ባይስማሙም፣ አንዳርጋቸው እንዲፈታ ሲሟገቱ የአንዳርጋቸው ድርጅት ግንቦት ሰባት ምን እያደረገ እንደሆነ የሚያውቅ ሰው ካለ መረጃዉን ያቀብለን። ግንቦት ሰባት ተንኮታኩቷል የምንለውም አንዱ ምክንያትእንግዲህ ይሄ ነው